## ሕገ-ወጥ ዕቃን የሚመለከት መረጃ አሰጣጥ፣ አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያ ለመወሰን የተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 1042/2017 ላይ የቀረበ ማብራሪያ

### 1. መግቢያ

በአለማችን ለመንግስታት ገቢ እና ለአገራት ሰላም እና ደህንነት ፈታኝ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ የሚገኘው በድንበር አካባቢ የሚከናወኑ ኮንትሮባንድን ጨምሮ ሕገ ወጥ ዕቃ ጋር የተያያዘ ንግድ ነው። ጉምሩክ እና የድንበር ቁጥጥር ስራ ላይ የተሰማሩ የመንግስት ተቋማት ኮንትሮባንድን እና ህገወጥ ንግድን በመከላከል ረገድ አጥጋቢ ስራን እንዳያከናውኑ ካደረጓቸው ምክንያቶች መካከል ኮንትሮባንዲስቶች የተጠናከረ አደረጃጀት ያላቸው እና በየጊዜው ተለዋዋጭ የሆነ የተወሳሰበ የኮንትሮባንድ ንግድ ዘይቤን የሚከተሉ መሆኑ፤ የአገራት ድንበር ርዝመት፤ ሙስና፤ የመንግስት አካላት አቅም ውስንነት እና በጦር መሳሪያ የተደራጁ አካላት ኮንትሮባንድን ዋነኛ የገቢ ምንጭ አድርገው መጠቀማቸው በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በአገራችን ኢትዮጵያም ከላይ በተዘረዘሩት ችግሮች ምክንያት የሕገ ወጥ ዕቃዎች ንግድ ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፋ በመምጣቱ የመንግስትን የቀረጥ እና ታክስ እንዲሁም የአገራችንን የውጭ ምንዛሪ ገቢ በማዳከም ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ ለሕገ ወጥ አካላት የገቢ ምንጭ በመሆን ለአገራችን ያለመረጋጋት አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል። በተጨማሪም በሕገ ወጥ ወደአገር የሚገቡ ደህንነታቸው ያልተረጋገጠ ሸቀጦች እና ፈዋሽነት የሌላቸው አስመስለው የተሰሩ መድኃኒቶች የህብረተሰቡን ጤና በመጉዳት እና ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ መስፋፋት እንቅፋት በመሆን ላይ ይገኛሉ።

በመሆኑም ህብረተሰቡ የሕገ ወጥ ዕቃዎች ንግድን በመዋጋት ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የችግሩን አሳሳቢነት በሚመለከት በቂ ትምህርት ከመስጠት በተጨማሪ ለማነቃቂያ እንዲሆን ወንጀሉን ለሚያጋልጡ ሰዎች የገንዘብ ወረታ መክፈል ይገባል። በሌላ በኩል በሕገ ወጥ ዕቃዎች ንግድ መስፋፋት ዋነኛ ምክንያት የህግ አስከባሪ አካላት አቅም ውስንነት በመሆኑ የተቋማቱን አቅም ማጠናከር የሚያስችል እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ይሆናል።

ይህንን አሳሳቢ ችግር መንግስት ብቻውን ለመቋቋም ስለማይችል የህብረተሰቡ እገዛ ወሳኝ ነው። የህገ ወጥ ዕቃዎች ዝውውር እና የማጭበርበር የንግድ ተግባራትን ለመከላከል የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ገንዘብ ሚኒስቴር ሕገ-ወጥ ዕቃን የሚመለከት መረጃ አሰጣጥ፣ አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያ ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ አዘጋጅቷል። ይህ መመሪያ ከዚህ በፊት በሥራ ላይ የነበረውን የመረጃ አቀራረብ፣ መውረስ እና ሽልማት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 78/2002ን በመተካት ሕገ ወጥ ዕቃዎች ጋር የተያያዙ ተግባራትን በመከላከል ረገድ ከመንግስት ጎን ለሚቆሙ ማበረታቻ የሚሰጥበትን እና ከኮንትሮባንድ እቃዎች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ በከፊል የህግ አስከባሪ አካላትን አቅም ለመገንባት ተግባር እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቷል። መመሪያው መረጃ ሰጪዎች ህገወጥ ዕቃዎች ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን የተመለከተ መረጃ አሰጣጥ አሰራርን ሥርዓትን ይዘረጋል፣ የማንነታቸውን ሚስጥራዊነት ይጠብቃል፣ መረጃን የማጣራት እና ዕቃዎችን ስለመያዝ እና የሽልማቶች አሰጣጥን በተመለከተ ግልጽ አሰራርን ያስቀምጣል።

## 2. የመመሪያው ተፈጻሚነት

መመሪያው የጉምሩክ እና ተያያዥ ሕጎችን በመተላለፍ፦

2.1 የአገሪቱን ህጎች በመጣስ ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር በሚገቡ እና ከአገር በሚወጡ እቃዎች (የከበሩ ማእድናትን ጨምሮ) እና እንስሣትን፤
2.2 በቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ ወደአገር ከገቡ በኋላ መብቱ ለሌለው ሰው የተላለፉ እቃዎችን፤
2.3 በህግ የተከለከሉ ወይም ገደብ የተደረጉባቸውን ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባት፣
2.4 በጊዜያዊነት ወደአገር ከገቡ በኋላ (በቱሪስት ስም የገቡትን ጨምሮ) በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሰው ያልወጡ ወይም ተገቢው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው እቃዎችን፤
2.5 በህገወጥ መንገድ ተከማችቶ ወይም ሲዘዋወር የውጭ አገር እና የኢትዮጵያ ገንዘብ፣ እንዲሁም የከበሩ ማዕድናት፡

መጠቆም እና መያዝን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 3. የጥቆማ አቀራረብ እና አመዘጋገብ

የሕገ ወጥ እቃዎችን ለሚጠቁሙ ሰዎች ተገቢውን ወረታ በመክፈል ረገድ ክፍተት ከታየባቸው አሰራሮች አንዱ የጥቆማው አቅራቢ ማንነት በትክክል ባለመመዝገቡ የሚፈጠር ችግር እንዲሁም ያለአግባብ ወረታውን ለማግኘት ሌሎች ሰዎችን ጠቋሚ እንደሆኑ አድርጎ ማስመዝገብ ነው፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል መመሪያው የጥቆማ አቀራረብን፤ አመዘጋገብን እና የጥቆማው ትክክለኛነት የሚረጋገጥበትን ስርአት ይዘረጋል፡፡

## 4. የጥቆማ መዝገብ እና ቅጾች

ጥቆማ በሚስጥር የሚከናወን እንደመሆኑ ጠቋሚዎች ጥቆማ የሚያቀርቡበትን ስርአት ከመዘርጋት በተጨማሪ ጥቆማው በወረቀት ወይም በኤሊክትሮኒክ ዘዴ የሚመዘገብባቸው ቅጾች እንዲኖሩ ማድረግ ተገቢውን መረጃ መያዝ የሚያስችል፤ በግልጽ የታወቀ እና ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር በማድረግ ህገወጥ አሰራሮችን መከላከል የሚያግዝ ይሆናል፡፡

በመሆኑም መመሪያው የጥቆማ መቀበያ ቅጽ፤ የጥቆማ መዝገብ እና የወረታ መቀበያ ቅጽ ሊኖር እንደሚገባ እና ይዘታቸውን ይወስናል፡፡

## 5. የጥቆማ ምስጢራዊነት

ጥቆማ እና የጠቋሚው ማንነት በሚስጥር ካልተያዙ የኮንትሮባንድ እቃው እንዲሸሽ እድል የሚፈጠር ከመሆኑም በላይ በጠቋሚው ደህንነት ላይ አደጋ ሊደርስ ይችላል፡፡ በመሆኑም ጠቋሚዎች ያለስጋት ጥቆማ ማቅረብ እንዲችሉ እና ጥቆማ የቀረበበትን ሕገ ወጥ እቃ  መያዝ እንዲቻል ሚስጢራዊነቱን መጠበቅ የሚያስችል የአሰራር ስርአት ሊኖር ይገባል፡፡

በመሆኑም የጥቆማነት ሚስጢራዊነት መጠበቅ የሚያስችል የአሰራር ስርአት በመመሪያው ተዘርግቷል፡፡

## 6. ጥቆማን ውድቅ ስለማድረግ

የወረታ ክፍያውን ለማግኘት ሲባል ሰዎች የሚታወቁ መረጃዎችን ወይም በበቂ ማስረጃ ያልተደገፉ መረጃዎችን በጥቆማ መልክ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመመሪያው የተዘረጋውን ስርአት ያልተከተለ ጥቆማ በማቅረብ ወረታ እንዲከፈላቸው ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

ይህንን ለመከላከል ተቀባይነት የሌላቸው ጥቆማዎች እንዲሁም ዋጋ የሌላቸው ጥቆማዎች በመመሪያው እንዲዘረዘሩ ተደርጓል፡፡

## 7. ሕገ ወጥ እቃዎችን ስለመያዝ

ሕገ ወጥ እቃዎችን መያዝ የሚችሉት የህግ አስከባሪ አካላት ብቻ ናቸው፡፡ ህግ አስከባሪ አካላት ሕገ ወጥ እቃን በሚይዙበት ጊዜ ሊከተሉት የሚገባውን አሰራር ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ መመሪያው ይህንን የሚወስኑ ድንጋጌዎችን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

## 8. የወሮታ ክፍያ አፈጻጸም

ለጠቋሚ እና ያዡች የወረታ ክፍያ የሚፈጸመው ከሕገ ወጥ እቃዎች ሽያጭ ከተገኘው ገቢ ወይም ከሚሰበሰበው ቀረጥ እና ታክስ ላይ መሆኑ በመመሪያው ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል የሕገ ወጥ ዕቃዎች ንግድን መከላከል የህግ አስከባሪ አካላት ባልደረቦች፣ የህዝብ ተመራጮች እና የመንግስት ሰራተኞች የመደበኛ ስራቸው አካል በመሆኑ ወረታ እንደማይከፈላቸው ግልጽ ተድርጓል፡፡

## 9. የወሮታ ክፍያ መጠን

በጠቋሚ መረጃ ሰጪነት ወደ አገር ሲገባ ወይም ከአገር ሲወጣ  የተያዘ ሕገ ወጥ እቃ በሚያዝበት ጊዜ ለጠቋሚ እና ለያዥ ወረታ ይከፈላል፡፡ የሚከፈለው ወረታ መጠን ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፦

- ለጠቋሚ 25% (ሀያ አምስት በመቶ)፤
- ለያዥ ህግ አስከባሪ አካላት 20% (ሀያ በመቶ)፤
- ሕገ-ወጥ ዕቃው የተያዘው በሚሊሺያ ከሆነ 10% (አስር በመቶ)፤
  እቃው የተያዘው በብሄራዊ መረጃ አገልግሎት ከሆነ 10% (አስር በመቶ) ነው፡

ለያዥ ህግ አስከባሪ አካላት እና ለብሄራዊ ደህንነት አገልግሎት የሚከፈለው የጠቋሚ እና የያዥ አበል በስራው ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች የሚከፈል ሳይሆን የተቋማቱን አቅም ለማጠናከር የሚውል ይሆናል፡፡ ይህም አሰራር ተቋማቱ የሚያገኙትን የወረታ ክፍያ የውስጥ አደረጀጀታቸውን ለማሟላት እንዲጠቀሙበት በማድረግ የሕገ ወጥ ዕቃዎች ዝውውር የመከላከል አቅማቸውን ለማጠናከር የሚያስችል ይሆናል፡፡